የሰ/መ/ቁ. 117907

ግንቦት 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሲርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካቾች - 1ኛ- ወ/ሮ ዘውዱ ፍቅሬ -

2ኛ- አቶ ኃ/ሚካኤል ተስፋየ 1ኛ } አመልካች በራሳቸው እና ስለ 2ኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ አበራ ጌታነህ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካቾች ላይ በአማራ ክልል ደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ሶስት የተለያዩ ጉዳዮችን በመያዝ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ለመከራከር የጥብቅና አገልግሎት ውል አድርገን ተገቢውን አገልግሎት የሰጠሁ ሲሆን በውሉ መሰረት ሊከፍሉኝ የሚገባውን አበል ያልከፈሉኝ በመሆኑ ብር 39,850.00 (ሰላሳ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ በጥብቅና ውሉ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት አልሰጠም፤ በክርክሩም ያስገኘልን ጥቅም የለም በመሆኑም የጠበቃ አበል ልንከፍል አይገባም፤ በአንፃሩ አገልግሎት ሳይሰጥ በመጀመሪያ ደረጃ ከፍያ የወሰደውን ብር 5,650.00 (አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ) እንዲመልስ እንዲወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ በዉሉ መሰረት አገልግሎት ሰጥቻለሁ ይበል እንጂ የቀረቡት ማስረጃዎች በተደረገው የጥብቅና ውል መሰረት እስከመጨረሻው አገልግሎት መስጠቱን የሚያስረዱ ባለመሆኑ የዳኝነት ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተከሳሾች የቅድሚያ ክፍያ ይመለስልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ጉዳዩ በይግባኝ በየደረጃው እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ የሰበር ችሎቱ በመጨረሻ ባሳለፈው ውሳኔ ተጠሪ ውል በተደረገባቸው በሶስቱም መዛግብቶች እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቅሬታ አቅርቦ የሰበር አቤቱታው አያስቀርብም ተብሎ የተዘጋ ስለመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፃፈው ደብዳቤ መረዳት

ይቻላል በማለት ተጠሪ ለሰጠው የጥብቅና አገልግሎት በቁርጥ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) አመልካቾች እንዲከፍሉት ወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች ነሀሴ 27/2007 ዓ.ም ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ግራ ቀኙም የስር ሙግታቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎት የጥብቅና አገልግሎት እንዲከፈል ባሳለፈው ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት ቢኖር በጭብጥነት ይዘን መርምረናል፡፡ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የጥብቅና አገልግሎት ውል ስለመደረጉና ስምምነቱም ተጠሪ ባለው የጥብቅና ሙያ ጉዳዩን እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከራከርላቸውና በአንፃሩ ለአገልግሎቱ የተጠቀሰውን ዋጋ ሊከፍሉ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካቾች የተሟላ አገልግሎት ባልተሰጠበት ብር 20,000.00 እንዲከፈል የክልሉ ሰበር ችሎት መወሰኑ የህግ ስህተት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በሙያው ደንብና ልማድ መሰረት ህግንና ማስረጃን ተንተርሶ እስከመጨረሻ ጉዳዩን በመከታተል በአፈፃፀም እንዲያገኙ ያደረግሁ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ማግኘት ከሚገባኝ ባነሰ ርትዕን መሰረት በማድረግ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ይዘዋቸው በነበሩ ሶስት የአመልካቾች ጉዳዮች እስከ ፌዴራሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበው የነበረ ስለመሆኑና ለሰበር አያስቀርብም በሚል የመ/ቁ 85890፤85891 እና 84464 የተዘጉ ስለመሆኑ ከፍርድ ቤቱ የተፃፈው ደብዳቤ ተጠቅሶ ከተሰጠው ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በገቡት ውል መሰረት እስከ መጨረሻ ድረስ ጉዳዩን ከተከታተሉ እና ከሙያቸው አንፃር እውቀትና ክህሎታቸውን ተጠቅመው አገልግሎት ከሰጡ የተፈለገው ውጤት ባለመምጣቱ ብቻ የተሟላ አገልግሎት አልሰጡም ሊሰኝ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ምንም አይነት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የውልም ሆነ የህግ መሰረት ስለሌለው የምንቀበለው አይሆንም፡፡ የነገሩ አጠቃላይ ሁኔታ ታይቶ ተጠሪ ለሰጠው የጥብቅና አገልግሎት በቁርጥ ብር 20,000.00 ይከፈል ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሚባል ህግ ስህተት ባለመኖሩም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45107 ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡